12/30/2016

ለኢትዮጵያ ምሁራን የተፃፈ ግልፅ ደብዳቤ

ወድ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ምሁራን ሆይ!

ኢትዮጵያ አገራችን ምጥ ላይ ናትና ትታደጓት ዘንድ ትማፀናችኋለች። የኢትዮጵያን አንድነትና ዕድገት፣ የህዝቦቿንም ሰላምና ብልፅግና የምትናፍቁ ዉድ ወንድሞቸና እህቶቸ የእናት ሃገር ጥሪ እነሆ ልበላችሁ። ለዚህ ትዉልድና ለሚመጡት ብዙ ትዉልዶች መስራች አባቶች (founding fathers) ትሆኑ ዘንድ ታሪክ የጣለባችሁን አደራ የምትወጡበት ጊዜው አሁን ነው። የቀደሙ አባቶቻችን ውድ ህይወታቸውን ለግሰው፣ ዳር ደንበራቸውን በአጥንታቸው አጥረው፣ በደማቸው አቅልመው ሰንደቅ አዉለብልበው አልፈዋል። ህግና ደንብ ሰርተው፣ ፊደል ቀርፀው፣ የዘመን መቁጠሪያ ቀመር ቀምረውና ሃይማኖት ተክለው፣ ታሪክና ባህል በብራና ፅፈው ለልጆቻቸው ትተው አልፈዋል።

ለዚህ የተቀደሰ ስራቸውም ታሪክ ከትዉልድ እስከ ትዉልድ ሲያወድሳቸውና ሲያወሳቸው ከሶስት ሽህ ዓመታት በላይ አስቆጥረዋል። ኢትዮጵያም ደንበሯ ተከብሮ፣ ታሪኳ ኩራት ሁኖን፣ ሃይማኖቷ አስተሳስሮን፣ ባህልና ልማዷም ኢትዮጵያዊ መጎናፀፊያችን ሁኖ ተሸምኖና ተሰንቆ ከእኛ ደረሰ። ሳይማሩ የተማሩት አባቶቻችንም እነርሱ ጦም እያደሩ የትምህርት ግብር ከፍለውና ስንቅ አመላልሰው አስተምረው አብርሆት ዘመን አድርሰዉናል።

የእኛ ዘመንና ትዉልድ ግን ታሪክ የጣለብንን አደራ ለቀጣዩ ትዉልድ ሳናስተላልፍ ግማሾቻችን በረሃብ፣ ከፊሎቻችን በእርስ በርስ ግጭትና እልቂት፣ የተረፍነውም በብሽታ እየተለቀምን በፈጠርነው ክፍተት አገራችን ለተተኪ ትዉልድ ሳናስረክብ ብኩን ሁነን የቀረን መሰለኝ።

የወያኔ/ኢህአዴግ መንግሥት ለራሱ የፖለቲካ ፍጆታ የደርግን ዘመን የህሊና ጠባሳ እየቀሰቀሰ እንደ ማስፈራሪያ በመጠቀም ለሃያ አምስት ዓመታት ኢትዮጵያን በዘር፣ በሃይማኖትና በጎሳ ከፋፍሎ ድብቅ አጀንዳ ካላቸው የዉጭ ኃይሎች ጋር በመተባበር አገሪቱን የባህር በር አልባ፣ ደንበሯንም ለሱዳን የእጅ መንሻ፣ ልጆቿንም ለዐረቡ ዓለም ዘመናዊ ባርነት ሸጦ፣ በየበረሃው ለሰው የአካል

መለዋወጫ እንዲቆራረጡና የአዉሬ ቀለብ እንዲነሆኑ አድርጎ፣ የቀረዉን ለጥይትና ለረሃብ ሰለባ ሲያደርገው ዝም ብሎ መመልከት ለምሁራኖቻችን የህሊና ቁስል ሊሆን ይገባል። አገዛዙ አንድ የዉጭ ወራሪ ኃይል ሊያደርገው ከሚገባው በላይ በራሱ ዜጎች ላይ የሚፈፅመዉን አረመኔያዊ በደል ዝም ብሎ መመልከት ኢትዮጵያዊ ባህሪ አልመስልህ አለኝ። ኢትዮጵያዉያን በአገዛዙ የሚፈፀምባቸዉን ግፍና መከራ ምሁራኖቻችን ተባብረው ሊያስቆሙት ሲችሉ ዝምታቸው አስደመመኝ። ኢትዮጵያም ከአንዱ መከራ ሳታገግም ወደ ሌላ መከራ ሳትወድ በግድ እየገባች ነው።

የወያኔን ግፈኛ መንግሥት ምንነት ተረድተው የመጨረሻ ፍርድ ለመስጠት ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ከምስራቅ እስከ ምዕራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ ሆ ብለው ተነስተው እየተፋለሙ ጥለው ሲወድቁ የምሁራኑ ዝምታ በተዘዋሪ የጠላታችን አጋዥ መስሎ እስኪታይ ግዑዝነቱ አስፈራኝ። የተቃዋሚ ኃይሎች ከአለፈው ጥፋታቸው ተመክሮ ገብይተው ትግላቸውን በማቀናጀት የህዝባቸዉን የመከራ ቀን ያሳጥሩ ዘንድ የምሁራኑ ሙሉ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። ተቃዋሚ ኃይሎች ዋናዉን ጠላት ወያኔን ወደ ጎን ትተው እርስ በእርስ ሲነናተሉ በህግ አምላክ ማለት የምሁራኑ ብቻ ሳይሆን የማንም ኢትዮጵያዊ ግዴታ ነው። የሚፈለገዉን ዓይነት የትግል አንድነት ለማምጣት የምክር አገልግሎት የሰጣችሁ ወይም መስጠት የምትችሉ ምሁራን እንደምትኖሩ አልጠራጠርም። ጊዜውም አሁን፣ የጥቂቶች ብቻ ሳይሆን የሁላችሁ ኃላፊነት ይሁን። ወያኔን ለማስወገድ በሰላማዊም ይሁን በትጥቅ ተደራጅቶ የሚታገል ማንም ድርጅት ከድል በኋላ ሊተገብረው የሚገባ ቁምነገር መኖሩን ማስጨበጥ ተገቢ ይመስለኛል። በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ህዝቡን የስልጣን ባለቤት እናደርጋለን የሚሉት ተቃዋሚ ድርጅቶች ከወዲሁ ዲሞክራሲን መለማመድና የገቡትን ቃል ኪዳን ዕዉን ማድረግ እንደሚኖርባቸው ጫና ማድረግ የምሁራኑ ድርሻ ነው። በአሁኑ ወቅት የህዝብ ድጋፍ ሊያገኙ የሚገባቸው ስብስቦች ይህን መሰል አጀንዳ ያላቸው ድርጅቶች ብቻ መሆናቸውንም በግብር ማሳየት ተገቢ ይመስለኛል።

ወጣም ወረደ፣ ወያኔና ግብረ አበሮቹ ከአሁን በኋላ ጥፋትን ሳይሆን ልማትን አመጣን፣ ሰይፋችን አንገት አልቆረጠም የአሸባሪዎች ወሬ ነው፣ ጦራችን በኢትዮጵያውያን ላይ ሳይሆን በጠላቶቻችን ላይ ነው የተቀሰረው በማለት

ማነንም ማታለልና እድሜ መቀጠል አይችሉም። ኢትዮጵያውያን ከዳር እስከ ዳር የወያኔን መርዛም እባብነት አዉቀው አናቱን ቀጥቅጠውና ስሩን ነቅለው ለመጣል በማያዳግም መልኩ ተነስተዋል። ፖለቲከኞችም በመሰላቸው ድርጅቶች እየመሰረቱ አንዳንድ ጊዜ እዉነተኛ ጠላታቸዉን ሌላ ጊዘ እርስ በእርሳቸው ሲጠፋፉና የጥፋቱ ሰለባ በመሆን እየወደቁና እየተነሱ ከዚህ የታሪክ መደምደሚያ ደርሰዋል። ህዝብን እየመሩ ሳይሆን ህዝብ እየመራቸውና የአንድነት አጀንዳ ቀርፆ እኛ አንድ ነን እናንተ ደግሞ አንድ መሆን አለባችሁ ሲላቸው ይደመጣል። ጆሮ ያለው ይስማ!!!

የትግሉ ጉዳይ በዚህ መልክ እልባት ከተሰጠውና የወያኔ ዉድቀት አይቀሬ ከሆነ ምንድን ነው ከኢትዮጵያ ምሁራን የምትፈልገው? የሚል ጥያቄ  ሊነሳ ይችላል። ጉዳዩ እንኳን ለእናንተ ለምሁራኖቹ ለማንም ግልፅ ነው። እኔና እናንተ ሶስት መንግሥታት አይተናል። የዘዉዳዊው የአፄ ኃ/ሥላሴ መንግሥት፣ የፋሺስቱ የደርግ መንግሥትና የዘረኛው የወያኔ/ኢህአዴግ መንግሥት። የማይከሰሰውና የማይወቀሰው የአፄ ኃ/ሥላሴ መንግሥት ያለ ተጠያቂነት ለአራት አስርተ ዓመታት ኢትዮጵያን ገዝቶ በግድ በህዝብ አመፅና በደርግ ሲወገድ በሰውና በንብረት ላይ የደረሰውን ጥፋት ታዉቃላችሁ። ደርግም በጥፋት ጀምሮ እድሜዉን በሙሉ ሲጨፈጭፍና ሲያጠፋ ኑሮ እራሱን በራሱ በልቶ በሩን ለወያኔ ከፍቶ ሰጠ። እሰየሁ እንኳን ለቀቀ። ወያኔ በተራው ማጥፋቱን በተራቀቀ መልኩ ቀጠለና ኢትዮጵያን አጥፍቶ ለመኖር እየተፍጨረጨረ ይገኛል። በግድ ካልተጨፈለቀና ብዙ ህዝብና ንብረት ካልወደመ እንደማይለቅ እናዉቃለን። መቸ ነው እኛ እንደሌሎች አገሮች ቢያንስ እንኳን  በሰላም ከአንድ መንግሥት ወደ እሚቀጥለው የምንሸጋገረው? አሁንም ለአስራ ሁለት ሰዓት እሩብ ጉዳይ ላይ የዓለማችን ታላላቅ መንግሥታት በፍሪካ ቀንድ ዙሪያ ያላቸዉን ይዞታ ላለመልቀቅ ሌላ አሻንጉሊት መንግሥስትና ስርዓት ቀርፀው ብቅ ይላሉ። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዉያን በዚህ በማይለካቸው ኪታ ዉስጥ በግድ እንዲገቡ ይገደዳሉ። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የነገሩ መሞቻ ይደርስና እንደገና የጥፋቱ ድግግሞሽ ይቀጥላል ማለት ነው። ከእናንተ የሚጠበቀው ይህን የጥፋት ድግግሞሽ የሚያስቀር ስርዓት እንድትሰሩ በአክብሮት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዉያን ይጠይቋችኋል።

የወደፊቷን ኢትዮጵያ በግልፅና ብሩህ መነፀር ተመልክታችሁ ልክ የበለፀጉት ሃገሮች መስራች አባቶች እያሉ የሚያስተዋዉቁንን ሰዎች መሰል ስራት ቅረፁልን ነው

የምላችሁ። ይህ ጉዳይ የፖለቲካ ሰዎችን አይመለከትም። የጥቅም ግጭት እንዳይፈጠር ከፖለቲካ ዉጭ ንፁህ ሞያ ያላችሁ ኢትዮጵያዉያን ምሁራን በአንድ ላይ ተነጋግራችሁና ተባብራችሁ፣ ጊዜም ወስዳችሁ ለአንድ ትዉልድ ብቻ ሳይሆን ለብዙ ኢትዮጵያዉያን ትዉልዶች የሚመጥን ሞዴል(model) ወይም ብሉ ፕሪንት(blue print) ቀርፃችሁ ብታቀርቡ ማንኛዉም የፖለቲካ ድርጅት ወይም መንግሥት በምርጫ መጥቶ የተፈቀደለትን ዘመን ጨርሶ አለማም አጠፋም ይለቃል ማለት ነው። እንደዚህ ከሆነ ኑረን ኑረን ወደ ጥፋትና እልቂት ዉስጥ አንገባም ማለት ነው። ከዚህ የበለጠ መስዕዋትነት ለሃገራችሁና ለወገናችሁ መስጠት አይጠበቅባችሁም። ለዚህም ህያውና አኩሪ ስራችሁ ታሪክ ተገቢ ክብርና ምስጋና እንደሚለግሳችሁ የምታዉቁት ሚስጥር ነው።

በእኔ አቅም ለዉይይት የማቀርባቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ከዚህ በታች ስዘረዝር እነዚህ ብቻ እንደማይሆኑ አምናለሁ።

1. መድብለ ፓርቲን የሚፈቅድና የሚጠቀም አጀንዳ ያቀረበውና በዜጎች የሚታመነው አሸንፎ ለተወሰነለት ዘመን አስተዳድሮ እየተጨበጨበለት እንዲለቅ የሚፈቅድ የፖለቲካ ስርዓት
2. የሚሻሻል እንጅ የማይሻር ህገ መንግሥት ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዉያን፣ ለመንግሥታቱና ለሠራዊቱም ጭምር ማበጀት። እስከአሁን በታሪካችን እንደታየው ከታዘዘ ሠራዊቱ የራሱን ወገን ያልጨፈጨፈበት ጊዜና ሁኔታ የለምና ከነዚህ ግዙፍ ኃይሎች በላይ ህግ እንዲሆን
3. ከአርባ ዓመታት በፊት የተነሳው የመሬት ስሪትም መልስ አላገኘምና የከተማና የገጠር የመሬት ስሪትን መልስ መስጠት
4. አገሪቱን ከድህነት የሚያወጣ የኢኮኖሚ ስርዓትና ኢትዮጵያዉያንን ከስደት የሚያስቀር ስልተ ምርት ማበጀት። በቅርብ እርቀት የሚደረስበት ዝቅተኛ የአንድ ሰው ገቢ በልቶ፣ ለብሶና ተጠልሎ እንዲኖር የሚያስችል ግብዓት ማስቀመጥ። በጤና ችግርና በእድሜ ጫና ጎዳና ላይ በልመና የሚኖሩትን የሚያካትት ዘዴ መቀየስ
5. የኃይል አቅርቦትን በሚገባ ማየት። ይህ በተለይ እንጨት በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚሰጠዉን አገልግሎትና በአሁኑ ጊዜ ከህዝብ ብዛት አንፃር ደኖች ሁሉ

ድራሻቸው እየጠፋ ስለሆነ እንጨትን የሚተካ የኃይል አቅርቦት ወይም እንጨትን እንደምርት ቆጥሮ የሚንቀሳቀስ ስርዓት

6. የተበታተነዉን የገጠር አኗኗር ስልጣኔ ማዳረስ እንዲቻል ወደ ትናንሽ ከተማ ቀመስ መንደሮች መለወጥ.......ወዘተ

መቸም አሁን ተግባብተናል። ማለት የፈለግሁትን አስፍታችሁና አብራርታችሁ በመረዳት ልክ አንድ አባት ወይም ትልቅ ወንድም/ እህት ታናሹ ሲኮላተፍ ጣፍጦትና አቃንቶ እንደሚሰማው አድርጋችሁ ስሙኝና ግዴታችሁን አሁኑኑ ተወጡ እላለሁ። ምንልባት ይህን ስራ እየሰራችሁ ያላችሁ ሰዎች ብትኖሩ በጥበት ሳይሆን በስፋት፣ በበቀል ሳይሆን በፍቅር ሁሉንም ኢትዮጵያዉያንንና ትልቋን ኢትዮጵያን በሰከነ አዕምሮ ተመልክታችሁ እናንተ እንደምትጠቀሙ ሳይሆን ፕሮጀክት ሰርታችሁ ሌላው እንዲጠቀምበት የምታቀርቡ ሁኖ ይሰማችሁ። እንደምታዉቁት ሁሉ ከፖለቲካው በማይተናነስ መልኩ የመሬት ጥያቄ ቁልፍ ጥያቄ ነው። መሬትን ተጠቅመው የሚኖሩት ወገኖቻችን በበሬ ጫንቃ በሚጎተት የእርሻ መሳሪያ መጠኑ አነስተኛና በጎርፍ የተጎዳ መሬትን አርሰው ለመቶ ሚሊዮን ህዝብ ቀለብ ለማቅረብ በጣም እየተቸገሩና ከተፈጥሮ ጋር እየተወራረዱ ስለሚኖሩ እንዴት ይቀጥል? የሚለዉንም አብራችሁ እዩት አደራ። የኢትዮጵያን አደራ ተቀብላችሁ አመርቂና የሚያኮራ ስራ እንደምትሰሩ በመተማመን ጠብና ጭቅጭቅን አስወግዶ ሰላምና አንድነት፣ ዕድገትና ብልፅግና የሚያጎናፅፍ ስርዓት እንደምታቀዳጁን ተስፋ በማድረግ በትህትና ስጠይቃችሁ በድፍረቴ ይቅርታችሁ አይነስብኝ። ጀግኖች ኢትዮጵያዉያን ጠላት በመረጠው የትግል ስልት ወያኔን ከጣሉና እናንተ ደግሞ ቀጣዩን ማንነታችን ካበጃችሁ፣ የሃይማኖት አባቶቻችን ደግም ለቢሔራዊ እርቅና ለቢሔራዊ ይቅርታ እንዲያዘጋጁን በዚሁ አጋጣሚ ማስታወስ እወዳለሁ። ጥያቄየን እንድትቀበሉና ጀምራችሁ እንድትፈፅሙ የእግዚአብሔር መልካም ፈቃዱ ይሁን።

አሜን!

አያልነህ ብርሃኑ ከአትላንታ

abirhanu@bellsouth.net or A-Birhanu@comcast.net